ዘመን ባንክ
Zemen
BANK

# የዘመን ባንክ አ.ማ

**የባለአክሲዮኖች 16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የስብሰባ ጥሪ**

## ለተከበራችሁ የዘመን ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 366(1)፣367(1) እና አንቀጽ 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ የተሻሻለው የመመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 12.1፣12.5 ፣13 እና አንቀጽ 14.1 መሠረት የዘመን ባንክ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 16ኛ አመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥቅምት 09 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ጀምሮ በሚሊኒየም አዳራሽ ስለሚካሄድ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጠቅላላ ጉባኤው ላይ እንድትገኙልን የባንኩ የዲሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

- የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ - አዲስ አበባ፣ ልደታ ክፍል ከተማ፣ወረዳ 07 ፣የቤ/ቁ ፡ አዲስ
- የባንኩ ዌብሳይት ፡ https://www.zemenbank.com
- የአክሲዮን ማህበሩ ምዝገባ ቁጥር - KK/AA/3/0002009/2005
- የአክሲዮን ማህበሩ ስም - ዘመን ባንክ አ.ማ
- የአክሲዮን ማህበሩ አይነት- በባንክ ስራ የተሰማራ
- የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ - 14,981,245,000.00
- የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ - 7,542,001,000.00

## የባለአክሲዮኖች 16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

1. እስከ መስከረም 29 ቀን 2017 ዓ.ም. ድረስ የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮችን ማሳወቅና ሪፖርቱን ተቀብሎ ማጽደቅ፣
2. እ.ኤ.አ. የ2023/24 በጀት ዓመት የዲሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥ እና በቀረበው ሪፖርት ላይ ተወያይቶ መወሰን ፣
3. እ.ኤ.አ. የ2023/24 በጀት ዓመት የዉጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥ፤ መወያየትና በቀረበው ሪፖርት ላይ መወሰን፣
4. እ.ኤ.አ የ2024/25 የኦዲት አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ በውጪ ኦዲተሮች በተጠየቀው የክፍያ ማሻሻያ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
5. እ.ኤ.አ. በ2023/24 በጀት ዓመት በተገኘ የተጣራ ትርፍ አደላደል ላይ በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
6. እ.ኤ.አ. የ2023/24 የዲሬክተሮች ቦርድን ከተጣራ ትርፍ ላይ የሚታሰብ ዓመታዊ የሥራ ዋጋ መወሰን፣
7. እ.ኤ.አ. የ2024/25 የዲሬክተሮች ቦርድ ወርሃዊ አበል መወሰን፣

## ማሳሰቢያ

1. በጉባኤው ላይ በአካል መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻቸው ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናው እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በባንኩ ዋና መ/ቤት 15ተኛ ፎቅ በሚገኘው ፋይናንስ እና ኢንቨስተርስ ግንኙነት መምሪያ በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በባንኩ የተዘጋጀውን የውክልና መስጫ ቅጽ ላይ በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን ፡፡ ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በባንኩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ መሆኑን እናሳውቃን ፡፡
2. የባንኩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጪ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡
3. ለተጨማሪ መረጃ ሰንጋ ተራ ራስ አበበ አረጋይ ጎዳና በሚገኘው የባንኩ ዋና መ/ቤት 15ኛ ፎቅ ፋይናንስ እና ኢንቨስተርስ ግንኙነት መምሪያ በአካል መቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር +251 115 54 00 53/66 ላይ መደወል ይችላሉ፡፡

**የዘመን ባንክ አ.ማ. - የዲሬክተሮች ቦርድ**

Call Center 6500
www.zemenbank.cominfo
@zemenbank.com

**የላቀ አገልግሎት ማዕከል**

